
ሚሽን ሞቢላይዜሽን ኢትዮጵያ አገልግሎት

# ስለወንጌሉ




## ክሊፍ ሚችል ቶም ዴቨርስ

## እስከ ሞት ድረስ እንኳ ለነፍሳቸው አልሳሱም

እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም።

የዮሐንስ ራእይ 12:11

በዶ/ር ግርማ በቀለ የተዘጋጀ

# እስከ ሞት ድረስ እንኳ ለነፍሳቸው አልሳሱም

ዕለተ MAY 9, 1936፣ ክሊፍ ሚችልና ቶም ዴቨርስ በቀድሞ የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ በጨካኝ የሽፍቶች ጦር አካላቸው ተበሳስቶ ሰማዕት የሆኑበት ቀን ነው። ሁለቱም ወጣቶች ነበሩ። ክሊፍ አውስትራሊያዊና የአንድ ሕፃን አባት ነበር። ዴቨርስ ካናዳዊና ለማግባት ዝግጅት ላይ ነበር። በወቅቱ አገራችን የፋሺስት ጣሊንን ወረራ በመጋፈጥ የጦርነት ዐውድማ ውስጥ ነበረች። ክሊፍ ባለቤቱንና አንድ ሕፃን ልጁን፣ ቶም ደግሞ እጮኛውን አዲስ አበባ ትተው ለወንጌል ሥራ ይርጋለም ነበሩ።

ክሊፍ የ ዮሐንስ ወንጌልን ወደ ጉጂ ቋንቋ የመተርጐም ሥራው ጫፍ አድርሷል። ቶም በክርስቶስ የተገኘውን ድነት ከውስጥ እየሰበቀ በሚወጣ ደስታና ግለት ይመሰክራል። በሞት ጥላም ውስጥም ሆነው፣ ልባቸው የተያዘው በወንጌል ሥራ ነበር። በጦርነት ግፍ በምትናወጠው አገራችን ውስጥ ነገ ምን ይዞ እንደሚመጣ በውል በማያውቁበትና የመኖር ዋስትና በሌለበት ስጋት ውስጥም ቢኖሩም፣ ዕለት ዕለት ልባቸው ይከብድ የነበረው በወንጌል ጉዳይ ነበር።

የጣሊያን ጭከና እየከፋ ሲመጣ ሚስዮናዊያን ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ቢታዘዝም እነዚህ ወጣቶች ለመታሰርና ለአንግልት ብቻ ሳይሆን ለመሞትም የቆረጡ ነበር። ለጌታ ወንጌል የነበራቸውን ሥር-ነቀል መታዘዝና ቁረጠኝነት ሳስብ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ከሦስት ዓመታት ቈይታ በኋላ የኤፌሶንን ቅዱሳን ሲሰናበት የተናገረውን የመጨረሻ ስንብት ያስታውሰኛል፦

"አሁንም እዚያ ስደርስ የሚደርስብኝን ባላውቅም፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንድሄድ ግድ እያለኝ ነው። ነገር ግን በምሄድባቸው ከተሞች ሁሉ እስራትና መከራ እንደሚጠብቀኝ መንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል። ይሁን እንጂ ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን ሩጫዬንና የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል የመመስከር አገልግሎቴን ብፈጽም፣ ለእኔ ሕይወቴ ከምንም እንደማይቈጠር እንደ ከንቱ ነገር ናት . . . እኔ መታሰር ቀርቶ ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም በኢየሩሳሌም ለመሞት እንኳን ዝግጁ ነኝ።" (ሐዋ. ሥራ. 21:22-24፤ 21:13)

ክሊፍ የቤተ ሰቡን፣ ቶም ደግሞ የእጮኛውን ደኅንነት ለማየት ዕለተ MAY 7, 1936 የይርጋለምን ቅዱሳን ተሰናብተው ከጥቂት አጃቢዎች ጋር የእግር ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ይጀምራሉ። ሆኖም ከሁለት ቀን አድካሚ የእግር ጉዞ በኋላ በመጨካኝ ሽማቂዎች በድንገት ተከበቡ። የሽፍቶቹን ልብ እንዲያራራና እንዲታደጋቸው እግዚአብሔርን አጥብቀው ለመኑ። መቼስ ክሊፍ ስለ ባለቤቱና አንድ ልጁ፣ ቶም ደግሞ ገና እንዳልፈነዳ የአበባ እምቡጥ የታመቀው የእጮኛው ፍቅር፣ የሠርግ ዕቅዳቸውና ተሰፋ ያደረገው ሕይወት የመጨለሙ ጉዳይ ምን ያህል ልባቸውን ሰንጐ እንደያዘው መገመት አይቻልም።

# እስከ ሞት ድረስ እንኳ ለነፍሳቸው አልሳሱም

እግዚአብሔር ዝም አለ። የመትረፍ ተስፋ ተሟጠጠ። የጉጂ ሽፍቶችም ጦራቸውን ሰበቁ፤ ያለርኅራኄም መንገደኞቹን ጨረሷቸው። በጦር ከተጨቀጨቀው ክሊፍ አስከሬን አጠገብ ጫፍ የደረሰው የዮሐንስ ወንጌል የትርጉም ሥራው ተበትኗል። ቢያንስ ይኸን እንኳን እንዲጨርስ እግዚአብሔር ለምን ጣልቃ አልገባም? የባለቤቱንና የአንድ ልጁን እንዲሁም የቶም አጮኛን የልብ ሰብራት ቃል ሊገልጠው እንደማይችል እያወቀ እንዴት አሰቻለው? ያውም በሰው አገር! መልስ የለኝም! ማንስ ማብራሪያ መስጠት ይችላል? እርሱ በሥራው ጻድቅና ፍጹም ነው ከማለት በስተቀር።

ሐዋርያው ጴጥሮስን የማምለጥ ተስፋ ከሌለው የጨካኙ የሄሮድስ እስር ቤት መልአኩን ልኮ የታደገው ያው እግዚአብሔር የሐዋርያው ያዕቆብ አንገት በሰይፍ ሲቀላ ዝም ብሏል። የዕብራዊ ጸሐፊም፣ በማይገባን መልኩ አንዳንዶቹን እግዚአብሔር ስለ መታደጉ፣ አንዳንዶቹን ደግሞ ዝም ስለማለቱ ምስጢራዊነት የደረሰበትን ድምዳሜ ሲያሰረዳ፣ በየትኛውም ኈራ ይሁኑ ስቅዩዎቹ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ፈቃድ በደስታ ታዘዋል። "ቢያድነንም ባያድነንም፣ በሕይወትም በሞትም የምንኖረው ለጌታ ነው"፣ በሚል ፍጹም የደስታ መታዘዝ!

“. . . የተሻለውን ትንሣኤ ለማግኘት ሲሉ፣ መትረፍን ንቀው ለሞት ለሚዳርግ ሥቃይ ራሳቸውን ሰጡ፤ ከዚህም ነጻ ለመውጣት አልፈለጉም። አንዳንዶቹ መዘባበቻ ሆኑ፤ ተገረፉ። ሌሎቹ ደግሞ ታሰረው ወደ ወህኒ ተጣሉ፤ በድንጋይ ተወገሩ፤ በመጋዝ ለሁለት ተሰነጠቁ፤ በሰይፍ ተወግተው ሞቱ፤ እየተኈሳቈሉ፣ እየተሰደዱና እየተንገላቱ የበግና የፍየል ቈዳ ለብሰው ዞሩ፤ ዓለም ለእነርሱ አልተገባቻቸውምና። በየበረሓውና በየተራራው፣ በየዋሻውና በየጉድጓዱ ተንከራተቱ።” (ዕብ. 11:35-38)

የባሏ ሞት ብቻ ሳይሆን እሟሟቱም የፈጠረውንና ዐጥንቷ ሥር ዘልቆ የገባውን የሐዘን ሰብራት በጸጋ በመታገሥ፣ የክሊፍ ባለቤት በዕለት ማስታወሻዋ እንዲህ ያላል፦

"ምንም አንኳን የፍቅር ሁሉ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ለምን በራሱ ሥራ ላይ ይተጉ የነበሩትን እነዚህን ሁለት ወጣቶች በአፍላ ዕድሜአቸው ሕይወታቸው እንዲቀጭ እንደ ፈቀደ ባይገባንም፣ ፍጹም ሉዓላዊ ፈቃዱን በጸጋ ልንቀበል፣ በፊቱም ልንሰግድ ይገባል . . . ክርስቶስን በሚመስል የከበረ ፍጻሜ በፊቱ ሰንቆም ያኔ ምስጢር የሆነብን ሁሉ ይገባናል . . . [ለባለቤቴ፣ ለቶምና አብረዋቸው ለነበሩ ወገኖች] በዚያ አስጨናቂና የጨለማ ሰዓት ልዩ የሆነና የማያልቅ የእግዚአብሔር ጸጋ እንደተትረፈረፈላቸው፣ እንዲሁም በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ የእርሱ የሆኑትን የማይከዳ እግዚአብሔር የዘላለም ዕድላቸውና ተስፋቸው መሆኑን በመረዳት በፍጹም ደስታ ወደሚወዱት ጌታ ዕቅፍ እንደገቡ ርገጠኛ ነኝ።" (ECLIPSE IN ETHIOPIA AND ITS CORONA GLORY, EDITED BY ESME RITCHIE RICE, 89)

# እስከ ሞት ድረስ እንኳ ለነፍሳቸው አልሳሱም

ወገኖች፣ በልባችን ያለውን ማጉርምረም እስቲ ልብ እንበል? እግዚአብሔር ምሕረት ያድርግልን!

አለን ሰሚዝ የክሊፍና የቶም የቅርብ ወዳጅና በይርጋለም የወንጌል አጋራቸው ነበር። ከሁለት ቀን በፊት ሲሰናበታቸው፣ ለመጨረሻ ጊዜ እንደነበረ በፍጹም አላወቀም። ስለ ክሊፍ የጻፈው ማስታወሻ እንዲህ ይነበባል፦

"ስለ ሚችል ልብ የሚነካ ምስክርነት አለኝ። ወደ ዘላለማዊ ቤቱ ከመሄዱ 12 ወራት በፊት ሌትና ቀን ይተጋ የነበረው የዮሐንስ ወንጌልን ለጉጂ ማኅበረሰብ መተርጐም ነበር። ፉሽስት ጨካኙ ጣሊያን በይርጋለም ላይ ቦንብ ሲያዘንብ የምንጠለልበት ምሽግ ውስጥም ቢሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስና የትርጉም ሥራው ከብብቱ አይለዩም ነበር። ያለምንም ማስጠንቀቂያ የጣሊያን አውሮፕላኖች ቦንብ በድንገት ሲያዘንቡብን፣ በአንዲት አንጡራ ነፍሱ ተወራርዶ ወደ ቤት በመሮጥ የትርጉም ሥራውንና መጽሐፍ ቅዱሱን ከቃጠሎ ያተርፍ እንደ ነበር የዐይን ምስክር ነኝ። በሽፍቶች በተገደለበት በዚያ የቀን ጨለማ ዕለት፣ በማጠናቀቅ ላይ የነበረው ትርጉም እስከሬኑ አጠገብ - ሲተረጉምላቸው የነበሩት ሰዎች እግር ሥር ነበር። የክርስቶስን ትሕትንና ርኅራኄ ልዩ በሆነ መልኩ ካየሁባቸው ጥቂት ሰዎች መካከል ክሊፍ ፊተኛው ነበር። የተሰበረ ትሑት ልብ የነበረው፣ አብዛኛዎቻችን ይቅር ለማለት የሚከብደንን በደል ይቅር ለማለት የማይቸገር፣ ቀራንዮ መስቀል ላይ የዋለው ክርስቶስ የሚነጸባረቅበት፣ ባገኘውም አጋጣሚ ሁሉ እርሱን የሰበከ . . ." (ECLIPSE IN ETHIOPIA, 89-90)።

ቅዱሳን፣ አሁን በጌታ ፊት ብንቆም ምን እያደረግን ይሆን ይምንገኘው? ሕይወታችንስ የቀራንዮን ክርስቶስ ያንጸባርቅ ይሆን? ወንጌላችንስ? ኖሩና ሞቱ፤ ወይስ ለጌታ ኖሩና ሞቱ እንባል ይሆን?

"እንግዲህ እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፣ ሸክም የሚሆንብንን ሁሉ፣ በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኀጢአት አስወግደን በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ።" ( ዕብ. 12:1 )

ቶምን በተመለከተ ደግሞ፣ ሰሚዝ እንዲህ በማለት ዝክሩን አስታውሷል፦

"ቶሚ የደስታ ሰው ነበር። የእግዚአብሔር ወሰን የለሽ ፍቅር የተገለጠበት፣ የኀጢአት ይቅርታና ድነት ያስገኘልን የመስቀሉ ሥራ እንዲሁም የክርስቶስ ዘላለማዊ ነጋሢነት ውስጡ ያለማቋረጥ ይፍለቀለቁ ነበር። የአገልግሎቱም ደስታና የውስጥ ግፊት ጉልበት ነበሩ። [ዳዊት፣ "አንተ ግን ቅዱሱ ነጋሢ፤ የእስራኤልም ምስጋና ነህ።" እንዳላው ማለቴ ነው! - መዝሙር 22:3]። ፍርሃት የለሽ፤ በተቃውሞም መካከል ጽኑ ነበር። በቶሮንቶ ከተማ መንገዶች ላይ ያለምንም ፍርሃት፣ ክርስቶስ የመላ ዓለሙ መድኅንና ጌታ መሆኑን ለመመስከር ይጓጓ እንደነበር ማሰብ አልቸገርም።

# እስከ ሞት ድረስ እንኳ ለነፍሳቸው አልሳሱም

በባለ አገሩ ይርጋለም ዘንድ እጅግ ተወዳጅ ነበር . . . እነዚህ ወንድሞች በታረደው በግ ክብርና ግርማዊ ውበት ውስጥ አሉ . . . እነርሱን ማጣት ትልቅ ሰብራትና የውስጥ ቁስል አምጥቶብናል። በተለይም ለቤተ ሰቦቻቸው። በእግዚአብሔር ጸጋ የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ዐይኖቻችን ካላቀኑ በስተቀር፣ ሕይወት ከምታመጣብን ጥልቅ ሐዘን የተነሣ እምነታችን የሚፈተንበት ወቅት አለ። በእንደ እነዚህ ዐይነት ጊዜ ነው፣ 'ሥጋዬና ልቤ ሊደክሙ ይችላሉ፤ እግዚአብሔር ግን የልቤ ብርታት፣ የዘላለም ዕድል ፈንታዬ ነው' ልንል የሚገባው።" (ECLIPSE IN ETHIOPIA, 90-91)።

ወንድሞችና እኅቶች፣ ወንጌል በእጃችን የገባው፣ በዐደራም የተጠበቀው በዚህ መልክ ነው። እኛስ በምን እንታሰብ ይሆን?

ክሊፍና ቶሚ እናመሰግናለን። በአገራችን የወንጌል ታሪክ መከራን የታገሣችሁ፣ ሕይወታችሁንም ስለ ወንጌል መሰዋዕት ያደረጋችሁ የገዛ ወገኖቻችንና እንዲሁም ከውጭ ሕዝባችሁንና ድሎትን ትታችሁ በታማኝነት ያገለገላችሁ ሁሉ፣ እናመሰግናለን። ብድራታችሁ ታላቅ ነው!

“እግዚአብሔር፥ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና። (ዕብ. 6:10)

TO ALL WHO ENDURED SUFFERING AND GAVE UP THEIR LIVES FOR THE SAKE OF THE GOSPEL IN ETHIOPIA AND BEYOND, THANK YOU!

“FOR GOD IS NOT UNJUST. HE WILL NOT FORGET YOUR WORK AND THE LOVE YOU HAVE SHOWN FOR HIS NAME AS YOU HAVE MINISTERED TO THE SAINTS AND CONTINUE TO DO SO." (HEB. 6:10)

ከብዙ አክብሮት እና ፍቅር ጋር!

እግዚአብሔር ሆይ፤ ለእኛ ደግሞ እንደ ክርስቶስ ወንጌል ባልኖርንበት ምሕረት አድርግልን፤ አድሰንም"

አሜን!
በ ዶክተር ግርማ በቀለ የተዘጋጀ፤